አፍሪካ ቲቪ

ከታላቁ ቁርአን
የመጨረሻዎቹ
‹‹የሶስቱ ክፍሎች››
ማብራሪያ
ዋና ዋቢ
ዙብደቱ ተፍሲር

# አፍሪካ አካዳሚ

**AFRICA ACADEMY**

www.AfricaAcademy.com



# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአቂዳ ትምህርት

በቴሌግራም

2

ሁለተኛው አለም አቀፍ የርቀት ትምህርት መሪ ቃል
“ትክክለኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው”

إِنَّ الدِّينَ عِندَ اللَّهِ الْإِسْلَامُ

“አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው ፡፡”

ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ
የአፍሪካ አካዳሚ
የርቀት ትምህርት
1441 ሒጅሪያ/2020

- ነጃ የሚወጣው ቡድን
- ከእሳት የሚድነውና ከቅጣት ነጣ የሚወጣው ቡድን የትኛው ቡድን ነው?
- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ፡- ‹‹ህዝቦቼ ሰባ ሶስት ቡድን ሆነው ይከፈላሉ፡፡ አንዷ ብቻ ስትቀር ሁሉም የእሳት ናቸው›› ሲሉ፡- ‹‹እነሱ እንማን ናቸው›› ተብለው ሲጠየቁ እኔና ባልደረቦቼ አሁን ያለንበትን መንገድ የተከተሉ ቡድኖች ብቻ ናቸው›› ብለዋል፡፡
- ስለዚህ እውነት ማለት ነቢዩን ባልደረቦቻቸውን የነበሩበትን ፈለግ መከተል ብቻ ነው፡፡ ከእሳት ነፃነት የምትፈልግና ስራህ ተቀባይነት እንዲኖረው ካሰብክ የሰለፎችን መንገድ ብቻ ተከተል እንጂ በዲን ውስጥ አዲስ ነገርን አትጨምር፡፡

- **ነጻ የሚወጣው ቡድን**
- **ከእሳት የሚድነውና ከቅጣት ነጣ የሚወጣው ቡድን የትኛው ቡድን ነው?**
- ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ፡- ‹‹ህዝቦቼ ሰባ ሶስት ቡድን ሆነው ይከፈላሉ፡፡ አንዱ ብቻ ስትቀር ሁሉም የእሳት ናቸው›› ሲሉ፡- ‹‹እነሱ እንማን ናቸው›› ተብለው ሲጠየቁ እኔና ባልደረቦቼ አሁን ያለንበትን መንገድ የተከተሉ ቡድኖች ብቻ ናቸው›› ብለዋል፡፡
- ስለዚህ እውነት ማለት ነቢዩን ባልደረቦቻቸውን የነበሩበትን ፈለግ መከተል ብቻ ነው፡፡ ከእሳት ነፃነት የምትፈልግና ስራህ ተቀባይነት እንዲኖረው ካሰብክ የሰለፎችን መንገድ ብቻ ተከተል እንጂ በዲን ውስጥ አዲስ ነገርን አትጨምር፡፡

- **የአህሉ ሱንና ወል ጀማዎች ስሞችና ባህሪያት**

አህሉ ሱና ወል ጀማዓ
ሱና ማለት በቋንቋ፡ መንገድ፤ ፈለግ፤ ልምድ፤ … ማለት ነው፡፡
ሕዝበ ሙስሊም መከፋፈል ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ይህ ስም የሚጠቀሰው ከቢድዓ ለራቀ፤ ተቃራኒ ሆኖ ለመጣ ሁሉ ነው፡፡ እናም አቶ እገሌ ‹ሱንይ› ነው ሲባል ተግባሩ በነብዩ ሙሐመድ (ﷺ)ትዕዛዝ መመሪያ መሠረት የሚሄድ ነው ማለት ነው፡፡
‹‹ጀመዓ›› ማለት ደግሞ ቡድን፤ ህብረት፤ ስብስብ፤.. ማለት ሲሆን ከሱና ጋር ተያይዞው ሲመጡ ቀደምት ሙስሊሞች /ሰሃባዎች/ እና ግልፅ የሆነ የቁርአንና የሐዲስን መመሪያዎችን ተከትለው የተጓዙ ቅን ተከታዮቻቸውን ያጠቃልላል፡፡ አብዱላህ ቢን መስዑድ፣ህብረት ማለት ብቻህንም ብትሆን እውነትን መከተል ነው’’ ብለዋል፡፡

- ስለዚህ ‹‹አህሉ ሱና ወል ጀመዓ›› ማለት የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባልደረቦችና ተከታዮቻቸው እስከ ምፅዓት ቀን የእነሱን ቀና መንገድ በፅናት የተከተሏቸው ሁሉ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ)ባልደረቦች ከታላቁ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የቁርኣንን ንባብ፣ ትርጉምና ጠቅላላ ይዘቱን የተረዱ ከመሆኑም አልፎ ቁርኣን የወረደበትን የዓረብኛ ቋንቋ ሥረ መሠረት ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው ነው፡፡

- አህሉ ሱና ወልጀመዓ ማለት መመሪያው ቁርኣን፣ሐዲስና የሙስሊም ሊቃውንት ስምምነት /ኢጅማዕ/ ለሆነ ሙስሊም ሁሉ ስም እንጂ በተወሰነ ጊዜ ለነበረ ቡድን የተሰጠ ልዩ ስም አይደለም፡፡
- የሰለፎች መሠረታዊ መመሪያዎቻቸው እና ዋና ዋናዎቹ መፅሐፍት
- ሰለፎች እምነት ላያ ያላቸው አቋም ከቁርኣንና ከሐዲስ ዝንፍ የማይል ነበር፡፡
- የሰለፎች እምነት ሲባል የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባልደረቦችና ተከታዮቻቸው የነበሩ ቀደምት ሙስሊሞች እምነትና በ212 ሒጅሪያ ላይ መእሙን የተባለው ኸሊፋ አስከመጣ ድረስ የነበሩበተ እምነት ነው፡፡

- **የሱና ባለቤቶች ዋና ዋና መርሆች**

የሱናና የህብረት ባለቤቶች መርሆ እምነት ብለው ከሚያስቀምጧቸው መሠረታዊ ነገሮች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

- ፤- እምነት ነክ የሆኑ ጉዳዮች ሁሉ ከቁርኣን፣ከንፁህ ሐዲስና ከሙስሊም ሊቃውንት የጋራ ስምምነት ብቻ መወሰድ እንዳለበትና በዚህ ጉዳይ ላይ ለሚነሱ ክርክሮችና ጥያቄዎች ሁሉ መልስና ዳኝነት ከቁርኣንና ከሐዲስ ጋር የተጣጣመ ብቻ መሆን እንዳለበት፣ ይህን የተፃረረ ግን ከዚህ በታች በተዘረዘረው መልክ ነው መታየት ያለበት፡፡
- 2-ነብዩ ሙሐመድ ( (ﷺያስተማሩትን ሐዲስ ሁሉ በንፁሕ፣ በአስተማማኝና በተጣራ ሰነድ ከተዘገቡ፣በአንድ የዘገባ ሰነድም ይሁን ከዚያም በላይ ቢሆን እውነት ነው ብሎ ማመንና አሚን ብሎ መቀበል
- 3-የቁርኣንና የሐዲስ ማብራሪያ ለመረዳት አንዱን የቁርኣን አያት ከሌሎች የቁርኣን አያዎች ጋር ወይም ከንፁህ ሐዲስ ጋር በማገናዘብ ቀደምት ሙስሊሞች፣እንዲሁም እነሱን በቅኑ መንገድ የተከተሉ የሃይማኖት ሊቃውንት በደረሱበት ፍችና በሰጡት ትንተና መሰረት እንጂ በቋንቋ ብቻ በመረዳት ስለ ቁርኣን የፈለጉትን ማለት እንደማይቻል፣
- 4-ለግል ስሜት /አስተያየት/ ሲባል ቁርኣንም ሆነ ሐዲስ የማይለወጥ መሆኑን ማመን ፣

- 5-ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ ከነብዩ ሙሐመድ ( (ﷺስለ ኢስላም ያላስተማሩት ነገር እንደሌለ፣ ከእሳቸው በኋላ ማንም ቢሆን ኢሰላም ላይ ሊጨምርም ሆነ ሊቀንስ እንዲሁም ሊያስተካከል እንደማይችልና ነብዩ ሙሐመድ( (ﷺያላስተማሩት ሃይማኖት ነክ ጉዳይ አለ ብሎ ማመን
- 6-የአላህ ቃልና የነብዩ ሙሐመድ ( (ﷺሐዲስ ለማንም አስተሳሰብና ለምንም ምክኒያት ተብሎ የማይታጠፍ የማይሻርና በማንም ሀሳብ የማይስተካከል ከፈጣሪ የወረደ ህግና መለኮታዊ መመሪ ነው ብሎ መቀበል፣
- 7-የጤናማ አእምሮ ምርምር ውጤት /ትክከለኛ ሳይንስ/ ከቁርኣንና ከሐዲስ ጋር በፍፁም እንደማይቃረን፣ ምናልባትም የሚያስጠረጥር ነገር ከተፈጠረ በቁርኣንና በሐዲስ የተነገረው እውነተ መሆኑን ማመን፣
- 8-የነብዩ ሙሐመድ ( (ﷺሰሃቦች ባደረባም ሆነ እነሱን በቅኑመንገድ የተከተሉ ሙስሊሞች ሁሉ በስህተት ነገር ላይ የማይተባበሩና የማይስማሙ መሆናቸውን ማመንና ቁጥራቸው የቱንም ያህል ቢያንስ እንኳን እውነትን የሚይዙ፣ ሐቅን የሚረዱ በየጊዜው እንደማይጠፉ ማመን፣
- 9-በሙስሊሞች መካከል ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች በሙሉ የዳኝነት ሙሉ ስልጣን ያለው ቁርኣንና ሐዲስ እንዲሁም የሊቃውንት ስምመነት እና ቂያስ ብቻ መሆኑ፣
- 10-ሃይማኖት ነክ ነገሮች ላይ በመልካም ዘዴና በጥሩ መንፈስ ካልሆነ በስተቀር መከራከርና ጥሩ አለመሆኑንና ሙስሊም በማያውቀው ነገር ላይ ሃሳብ መስጠት እንደሌለበት ማመን፣"(እርሱ) የሚያዛችሁ በኃጢአትና በጸያፍ ነገር በአላህም ላይ የማታውቁትን እንድትናገሩ ብቻ ነው"

"ትክክለኛው ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነው"